# ያንተ አባት ዶ’ፍተሩ

(ከሂኖክ ታ. የሺጥላ)

ያንተ አባት ዶ’ፍተሩ፣
ምላሱ ጡሩሩ.......
ወኔው.....እስክርቢቶ....
ካ’አማሪካ ጫካ.....
ከዋሻው ውሰጥ ገብቶ......
በፓል....ሽሙር.....ትግል.....
ሃገር አስለቅቆ.....ደምንም ተቃብቶ......
......በድንቅ እንቶ ፈንቶ.......

ዘዴውን አርቅቆ.......
በከረባት ታንቆ.........

እዩት ሲንጎማለል......
ሀምሳ ግዜ ሲክድ.....
ሀምሳ ግዜ ሲምል........

ያንተ አባት ዶ’ፍተሩ፣
በሱፍ ስልቻ ውስጥ ....አካሉን ወጥቆ.....
ማቃጠር....ነው ክብሩ......
እሱ ነው እምነቱ.......
ነጻ ወንድነቱ........
እሳት በሌለበት......
ወርቅ አንጣሪነቱ.......
እሱ ነው ጉልበቱ......
ያንተ አባት ዶ’ፍተሩ
ደርሶ....ተንደርዳሪ......
ለናት ሀገር ምድሩ.....የወሬ ተጠሪ.......
ባህር ማዶ ተጉዋዥ......ጦር አጠናካሪ......
.....እራሱን የሾመ.....ድንቅ አደራዳሪ......

ያንተ አባት ዶ’ፍተሩ፣
......ፈረንጂኛ.......ክብሩ......
ክህደት ድንበሩ.....
ቦርሳ ማንጠልጠሉ....
እርፍና ሞፈሩ....
ጠጉር ማበጠሩ....
ቀበቶ...መሸምቀቅ....
ወገሉ...ቀ’ምበሩ....
ያንተ አባት ዶ’ፍተሩ
......ፈረንጂኛ.......ክብሩ......
ሃገር....ለመገንጠል.....
ሕዝብ ለመነጠል......
በሱፍ ስልቻ ውስጥ ....አካሉን ወጥቆ.....
ዘመን መዳከሩ.......
ያስብለው ከሆነ......ምሁሩ......

.....

ያንተ አባት ዶፍተሩ...
እንደምን አደሩ?